# ከሠርቶ አደር: ወደ ሰርቆ አደር፤ ነገስ ??!!

## " ያ ባሌ ሽረሪቲ - ነምኒ ሃቱ ነማ ሚቲ ! "

( አሥራደው ከፈረንሳይ )








ማስታወሻ :

ወያኔዎች አገራችን ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት ሲያስርቡን ቆይተው፤ ጠ/ምኒስትር አብይ አህመድና አቦ ለማ መገርሳ የአገራችን አትዮጵያን ስም ደጋግመው በመጥራት በመጠኑም ቢሆን ከርሃባችን ስላስታገሱን ምስጋና ቢገባቸውም፤ የዘርና የጎሳ ፖለቲካ: ያመጣብንን ውርደትና: ክስረት እያወቁ፤ ዘርና ጎሳን መሰሠረት ያደረገ: የፖለቲካ ስብስብ ማስቀረት ሲችሉ፤ በዚያው ለኢትዮጵያ ህልውና አስጊና፤ አጥፊ በሆነ ጎዳና እንዲቀጥል መፍቀዳቸው፤ ( መፈለጋቸው) አንድም: ተራው የ'ኛ ነው በሚል እሳቤ፤ ሁለትም: ህወሃት እንዳይቀየማቸው ፈርተው ይሆን ?!

መንደርደርያ :

- " Derrière toute grande fortune se cache un grand crime.
Honore de Balzac"

" ከማንኛውም የተከማቸ ሃብት በስተጀርባ: የተደበቀ ትልቅ ወንጀል አለ "
ኦኖሬ ባልዛክ

- " Il n'y a pas de mouvais herbe s'il n'ya pas le mouvais Cultivateur "

Victor Hugo

" መጥፎ  ዘሪ (የሚዘራ) ከሌለ መጥፎ ሳር አይበቅልም "
ቪክቶር ሁጎ

- Little thieves are hanged but great ones escape.
*14th Century French Proverb*
"ትንንሾቹ ሌቦች ሲታነቁ (ሲያዙ) ትልልቆቹ ሌቦች አመለጡ"
ከ14ኛው ክፍለ ዘመን የፈረንሳይ ህዝብ አባባሎች

- “ On peut pardonner, mais oublier, c’est impossible.”
Honoré de Balzac

" ይቅር ማለት ይቻል ይሆናል፤ መርሳት ግን አይቻልም "
ኦኖሬ ባልዛክ

- “ Lead from the back — and let others believe they are in front. ”
Nelson Mandela

" ከኋላ ሆነህ በመምራት፤ ሌሎች ከፊት መሆናቸውን ይመኑ "
ኔልሰን ማንዴላ

- " I will not let anyone walk through my mind with their dirty feet."
Mahatma Gandhi

" ማንንም በቆሻሻ እግሮቹ በአይምሮዬ ውስጥ እንዲመላለስ አልፈቅም "

መሃተማ ጋንዲ

Live as if you were to die tomorrow. Learn as if you were to live forever.

Mahatma Gandhi

" ነገ እንደምትሞት ሆነህ እየኖርክ፤ ለሁልጊዜ እንደሚኖር እየሆንክ ተማር "
መሃተማ ጋንዲ

መግቢያ :

የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮን ሳይኖራት በቀዳዳ ብቻ እያጮለቀ በመመልከ ይኸው 27 ዓመታትን አስቆጠረ:: ባለ ጊዜዎች ከበሯቸውን በመደለቅ፤ እንጣጥ: እንጣጥ: እያሉ ሲጨፍሩ፤ ሕዝባችን የጆሮዎቹን ብራና እያስጠለዘ ለ27 ዓመታት ደጅ ጠና:: ሊያሸተው እንጂ ሊቀምሰው ባልታደለ የነሱ የምግብ ሽታ ምች እየተመታ ለ27 ዓመታት ታመመ:: ከደደቢት በረሃ በባዶ እግራቸው አዲስ አበባ እንዳልገቡ፤ በመኪና: በቢጋ አቧራ እያቦነኑበት፤ በክረምት: ቆሻሻ ውሃ እየረጬበት በሕዝባችን ተሳለቁ :: እነሱ በአገራችን ሃብት: አውሮፓና አሜሪካ ልጆቻቸውን እየላኩ ሲያስተምሩ፤ የኛ ልጆች ለአረብ አገራት ግርድናና አሽከርነት ተዳረጉ:: ጠዋት ማታ የምትርበን አገራችን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፤ ጩቅላ ሕፃናትን ሳይቀር፤ ያለ ርህራሄ በማን አለብኝነት እየሸጡ ደንደሳቸውን አደለቡ:: ትውልድ ገዳይ የሆነ ስርዓተ ትምህርት በመቅረጽ፤ ለ27 ዓመታት አዲሱን ትውልድ አመከኑ:: ይባስ ብለው ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤ ትምህርታቸውን ጨርሰው የተመረቁ ወጣቶችን የድንጋይ (Cobble stones) ጠራቢ በማድረግ፤ ለምንግዜም የማይሽር የህሊና ስብራት በወጣቱ ላይ ፈጸሙ::

ይህን ያደረጉት: ሆን ብለው በወጣቱ አይምሮው ውስጥ: የማይሽር ጠባሳ በመፍጠር፤ የበታችነት ስሜትን ተቀብሎ: እሺ ብሎ አጎንብሶ እንዲኖር ለማድረግ ነበር :: ግን አልተሳካላቸውም !!

" ሂድ አትበለው ግን እንዲሄድ አድርገው " እያሉ ብዙ ዜጎች አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ አድርገዋል:: የአባቶቻችንና: የአያቶቻችንን መቃብር ሳይቀር: ቆፍረው አጽም እያወጡ መሬቱን ቸብችበዋል:: ከስኳር ሽያጭ ጥቅም ለማግበስበስ ሲሉ ገዳማትን አሳርሰው መነኮሳትን ወደ ወህኒ ቤት

ወርውረዋል:: በጥቅሉ በሰብአዊ መብት ጥሰት፤ በሌብነት፤ በመሬት ዝርፊያ፤ በስልጣን ብልጊያ........ወዘተ. በኢትዮጵያ ሕዝብና ምድር ላይ በወያኔዎች ያልተፈጸመ ግፍ የለም ::

እንዲያም ሆኖ፤ ኢትዮጵያ አልጠፋችም፤ ሕዝቡም በዕምነቱ ጸንቶ: በአገር ውስጥና: ከአገር ውጪ ያለው ሕዝባችን፤ ትግሉን በማፋፋም: አሁን ያለበንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: አሁንም በሽርፍራፊ ድሎች ሳንዘናጋ: የተጀመረውን ትግል በመቀጠል: ከግቡ ለማድረስ እጅ ለእጅ ተያይዘን: መጓዝ ይኖርብናል::

ቀደም ብሎ የወታደሩ አገዛዝ (ደርግ)፤ ቀጥሎ ደግሞ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ድል በተከታታይ ነጥቀዋል:: ከአሁን በኋላ የምናስነጥቀው ድል ሊኖር አይገባም:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል አንድ ጻድቅ ወይም አንድ የኛ የሆነ ሙሴ ስለማይታጣ፤ ፈጣሪ ኢትዮጵያን እንደ እያሪኮ እንደማያጠፋት: ዕምነታችን ጥኑ ነው ::

ለ27 ዓመታት: በኢትዮጵያ መስረቅ የሚያስከብር፤ መሥራት የሚያሳፍር ሆኖ፤ ሌቦች በጠራራ ፀሐይ ሻኝቸውን አሳብጠው እየተንግለሉ ተዝናንተውብናል:: በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሌባ! ሌባ! ተብሎ እየተሰደበ የሚገዛ መንግሥት ያየነው ወያኔን ብቻ ነው:: እነሱም ሌብነቱን አምነውበት፤ ስርቆታቸውን በመቀጠል፤ በአገራችን ታሪክ: ታይቶና ተደርጎ በማይታወቅ መልኩ፤ ከብሔራዊ ባንክ ወርቅ ዘርፈው፤ የባሌስትራ ብረት ከምረውልን ሄረዋል:: የዘረፋውን ዓይነት፤......... የግድያውን፤........ የእስሩን፤...... የማሳደዱን፤...... የመሬት ችብቸባውን፤......... ወዘተ. ዝርዝር ለመግለጽ ቦታ ስለማይበቃኝ ትቸዋለሁ ::

" የሌባ ዐይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ " እንዲሉ፤ የትናንት ሌቦቻችን ይባስ ብለው፤ ትግራይ ክፍለ ሃገርን የሌቦች ዋሻ በማድረግ፤ ሌብነታቸውን በሌቦች ህግ ለማጽደቅ መንጫጫት ይዘዋል:: እዚህ ላይ ስደርስ በልጅነቴ በሲኒማ ኢትዮጵያ ያየሁት፤ አሊባባና 40 ሌቦች (Ali baba and the fortinght thieves) የሚለው ፊልም ትዝ አለኝ::

አሁን ደግሞ: በዚህ ሽውራራ ዘመን፤ በኢትዮጵያ: ህወሃትና ሌቦቹ (TPLF and its thieves) ትግራይን የሌቦች ዋሻ በማድረግ፤ የትግራይን ሕዝብ ለሌብነታቸው አጋር እንዲሆን፤ ጠዋት ማታ ደጅ መጥናት ይዘዋል:: የህወሃት ሌቦች ያልተረዱት ነገር ቢኖር፤ የትግራይ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፤ ሌቦችን በእጅጉ የሚጠየፉ: ለሃይማኖታቸው ጽኑ፤ ለአገራቸው ቀናኢ፤ ለወገኖቻቸው ፍቅር የተላበሱ፤ ንጹህ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው:: በመሆኑም: የትግራይ ሕዝብ ሌቦችን በጉያው ውስጥ ሸጉጦ፤ ታሪኩን እንደማያበላሽ ሙሉ በሙሉ እንተማመናለን::

ዱሮ: ዱሮ፤ በአገራችን ሌባ በፈጸመው አጠያፊ ድርጊት፤ የሰው ዓይን ለማየት ድፍረት አልነበረውም :: ሌባ መንግሥት: የሚያፈራው ሌባ ትውልድ በመሆኑ፤ ዛሬ: ዛሬ ወያኔ (ህወሃት) ለ27 ዓመታት የፈለፈላቸው ሌቦች: ይሉኝታ የማያውቁ፤ ዓይን ቀቅለው የበሉ ሃፍረተ ቢሶች በመሆናቸው፤

ዝረፍ ልጄ ! - ዝረፍ ልጄ !

መማር ዋጋ የለው- ሃብት ሞልቷል በጄ !!

በማለት ወገኖቻቸውን እያስራቡ የዘረፉትን የአገር ሃብት፤ ደከመው ያፈሩት በማስመሰል ዐይናቸውን በጨው ታጥበው፤ ይመጻደቁብናል:: በሠርቶ አደር 17 ዓመታት፤ በሰርቆ አደሮች 27 ዓመታት ፈጀን፤ ነገስ ወዴት ይሆን የኛ ጉዞ ??!!

ጎበዝ ! ከአሁን በኋላ ውሻን ውሻ፤ ድመትን ድመት የምንልበት ዘመን ላይ በመሆናችን፤ ሌባን: ሌባ፤ ዘራፊን: ዘራፊ በማለት ስማቸውን እየጠራን ለፍርድ እንዲቀርቡ፤ ሌት ተቀን ተግተን በመሥራት የተዘረፈውን የአገራችን ሃብት ለማስመለስ ሁላችንም በያለንበት፤ አገርቤት ያለው በአገርቤት፤ በውጭ አገር ያለን ኢትዮጵያውያን በያለንበት አገር፤ ሌቦችን እንቅልፍ ማሳጣት ይኖርብናል ።

የጎሳና የዘር ፖለቲከኞች: የኢትዮጵያን ሕዝብ የመብት፤የነፃነት፤ የወንድማማችነትና፤ በእኩልነት አብሮ የመኖር ፍላጎትና: ሚዛናዊ የሃብት ክፍፍል ጥያቄዎችን: በሸውራራ መነጥር መመልከታቸውን ዛሬውኑ ካላቆሙ፤ ወያኔን የበላች ውሻ: እነሱንም መዘንጥልዋ እንደማይቀር: ከወዲሁ ይወቁት። የኛ ችግር: ፍትህ፤ እኩልነት፤ ነፃነት፤ ዕድገትና ሚዛንያዊ የሃብት ክፍፍል፤ በጥቅሉ የዲሞክራሲ እጦት እንጂ ጎሰኝነትና ዘረኝነት አይደለምና !!

ሌላው: የኢትዮጵያ ሕዝብ: ፖለቲከኞችን በእጅጉ ያቀብጣል። ዛሬውኑ እላይ ይሰቅልና፤ ነገ መልሶ ከሰቀለበት አውርዶ መሬት ላይ ይፈጠፍጣቸዋል። ለምሳሌ: መንሥቱ ኃ/ ማርያምን: "ቆራጡ መሪ፤ ሲል ቆይቶ፤ ቀጥሎ ወደ ሃራሬ ፈረጠጠ" አለው፤ ልደቱ አያሌውን: "ኢትዮጵያዊው ማንዴላ ብሎ ባቆላመጠ ማግስት፤ ልደቱ ክደቱ" ብሎ አጮለው፤ (ልደቱስ በሥራው ነው)...... ሌላም ሌላም። ነገ ደግሞ የለማ መገርሳና የአብይ አህመድ ተራ ላለመሆኑ ምን ዋስትና አለ?! እናም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፖለቲከኞችን የማቅበጥ አባዜውን ማቆም ይኖርበታል። ለምሳሌ ጠ/ምኒስትር አብይ አህመድን ለመጥራት፤ ዶ/ር የሚለውን የትምህርት ማዕረግ አግተልትሎ ማቅረቡ ከንቱ ውዳሴ ነው። በኔ ዕምነት ጠ/ምኒስትር አብይ አህመድ፤ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚወክሉበት በከፍተኛ የማዕረግ ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው፤ የኢትዮጵያ ጠ/ ምኒስትር ተብለው ከመጠራት ውጪ፤ ሌላ የሚያስከብራቸው ማዕረግ የለም። እሳቸውም ቢጠየቁ፤ ከዚህ የተለየ መልስ እንደማይሰጡ እርግጠኛ ነኝ። እናም: ይታሰብበት!!

<u>በቋጫ</u> :

ጣሊያን እስከ አፍንጫው ድረስ ታጥቆ ለ5 ዓመታት በዱር በገደሉ አበሳውን እያየ፤ ቅኝ ሊገዛው ያልቻለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የጣሊያን ሹም ባሽና ቡልቅ ባሽ፤ የልጅ ልጆች: እንዴት ቀጥቅጠውና ዘርፈው ለ27 ዓመታት ሊገዙት ቻሉ ?!

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመሻት ልሂቅ መሆን አያሻም፤ ጣሊያን ያልተሳካለት ከኛ የተለየ ቀለምና ሃይማኖት ስለነበረው ብቻ ሳይሆን፤ የአገሩ ፍቅር በልቡ እንደትኩስ እሳት የሚነድ፤ ማርያምን ወይም ጊዮርጊስን ካለ ለጓደኛው ሚች፤ ሃይማኖተ ጥኑ፤ አገር ወዳድና ጀግኖች የነበሩ አባቶችና አያቶች ስለነበሩን ነው ። በነሱ መስዋእትነት ነው፤ የቅኝ ገዢዎች እርግጫ ሳናይ ነፃ አገር የተረከብነው።

የዛሬው ትውልድ የገዛ አገሩን ታሪክ በፈረንጅ ላፒስ ፈግፍጎ በማጥፋት እየተደናበረ፤ የመጣበት ታሪክ ጠፍቶት፤ ዛሬን ሳይኖራት፤ ለነገ እቅድ ሳይተልም: እንዲሁ ይባዝናል። ለዚህ ምክንያቱ፤ በጎሳና በዘር ከፋፍለው፤ እንደ ቤት እንስሳ በክልል ከለለው፤ እንግዛህ ሲሉት፤ እንደ አያትና ቅድም አያቶቹ እንቢኝ ማለት ስላቃተው ነው ወያኔዎች ለ27 ዓመታት ቀጥቅጠው፤ ዘርፈውና አዋርደው ሊገዙት የቻሉት ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን የተሳሰርንበት ገመድ፤ የተጎናጎነና: ደንዳና በመሆኑ፤ በጎሳና በዘር ፖለቲከኞች ሴራ አብሮነታችን አይበጠስም።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!
ታህሳስ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ( December 14/2018 )